# ጋዜጣዊ መግለጫ

የአሜሪካ ኤምባሲ፤
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
*2015/06*

ለተጨማሪ መረጃ ቀጥሎ በተመለከተው ቁጥር ይደውሉ፡-011-130-7033
ድረ-ገጽ፡- http://ethiopia.usembassy.gov

---

## የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ከ100 በላይ ሴቶችን በንግድሥራ ፈጠራና በአመራር ጥበብ አስመረቀ

### *ሥልጠናው በእንስሳት እርባታ ዘርፍ እምቅ የአመራር አቅም ያላቸው  ሴቶች ላይ ያተኮረ ነው*

*አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ፤የካቲት 22 ቀን 2007 ዓ.ም.፡-የአሜሪካ መንግሥት በዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲው(USAID) በኩል በንግድ ሥራ ፈጠራና በእንስሳት እርባታ አመራር ያሠለጠናቸውን 107 ሴቶች ዛሬ አስመረቀ፡፡ ሠልጣኞቹ ከአማራ፣ከኦሮሚያ፣ከደቡብና ትግራይ ክልሎች የተውጣጡ ናቸው፡፡ ሥልጠናው በቴክኒክ፣ንግድ ተኮርና በክትትል የማብቃት ክህሎቶች ላይ ያተኮረ በመሆኑ፤ሴት ተመራቂዎች ስኬታማ የንግድ ሥራ አንቀሳቃሾችና በየአካባቢያቸው የሚገኙ ተመሳሳይ ዝንባሌ ያላቸውን ሌሎች ሴቶች ማገዝ የሚችሉበትን ብቃት ያጎናፅፋቸዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ለዚህ የአምስት ወር የሥልጠና መርሀ ግብር እገዛ ያደረገው በግብርና ምርት ዕድገት መርሀ ግብር የእንስሳት ገበያ ልማት በኩል በሚያካሂደው እንቅስቃሴ ነው፡፡*

*በአብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ሴቶች እንስሳት  ማደለብና መመገብን ጨምሮ በተለያዩ የእንስሳት እርባታ ሥራዎች የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ምንም እንኳን እነዚህ ሴቶች በስፋት የእንስሳት መኖ በማቅረብ፣ወተት በማለብ፣በረት በማጽዳት፣ወተትና የወተት ተዋጽኦዎችን በማቀነባበርና በመሸጥ ቢሳተፉም፤ተጨማሪ እሴት  በሚያስገኙ እንቅስቃሴዎች የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ዝቅተኛ በመሆኑ ከእንስሳት ዘርፍ ልማት የጎላ አስተዋጽኦ እንዳያደርጉ ገድቧቸዋል፡፡*

*የኢትዮጵያ መንግሥት ከፆታዊ ልዩነት የሚመነጩና በእንስሳት ንግድ ዘርፍ የሚንፀባረቁ የምርታማነት፣የትርፋማነት፣የተሳታፊነትና የአመራር ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያደርገውን ጥረት የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ በመደገፍ ላይ ይገኛል፡፡ ስለሆነም የዛሬዎቹ ተመራቂዎች ባገኙት ሥልጠና ተጠቅመው ለሌሎች አርአያ እንደሚሆኑ ከመታመኑም በላይ*

፤በየአካባቢያቸው የሚገኙ ሴቶችን በዘርፉ በማሠልጠንና ተከታትሎ በማብቃት ተፅዕኖ ፈጣሪም እንደሚሆኑ ይጠበቃል።

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ በአሜሪካ መንግሥት መጪውን ትውልድ መመገብ የተሰኘ መርሀ ግብር ሥር ይህን ሴቶች ላይ ያተኮረና በእንስሳት እርባታው ዘርፍ ያለው የእሴት ሠንሰለት ምርታማነትና ተወዳዳሪነትን በማሻሻል እንዲጠናከር እያደረገ ሲሆን፤በተለይም በዘርፉ የንግድ ሥራ ፈጠራ እምቅ አቅም ያላቸው አልያም የንግድ ሥራ ፈጣሪና በአርአያነታቸው የሚጠቀሱ ሴቶች ላይ በማተኮር የሥልጠና ዕድል ያመቻችላቸዋል። የዛሬ ተመራቂዎችን ጨምሮ እስካሁን በንግድ ሥራ ፈጠራና በአመራር ጥበብ 211 ሴቶች የዕድሉ ተጠቃሚ ሆነዋል።

###